# Grenfell Tower community update: February 2026 - Amhraic / አማርኛ

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፦ ፌብሩዋሪ 2026**

ግሬንፌል ታወር በአደጋው ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ጥልቅ የሆነ የግል ትርጉም እንዳለው እና ቦታው ለቤተሰቦች የተከበረ መሆኑን እንረዳለን።

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራችንን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን ልናጋራዎ እንወዳለን። በዚህ ወቅታዊ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይችላሉ፦

- ክሬኑን ዝቅ የማድረግ ሂደት
- የግሬንፌል (Grenfell) የልብ ቅርጽ ባነሮች
- የታወሩ መብራቶች
- ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና ጫጫታ የሚደረግ ክትትል መረጃ
- የጤና እና ደህንነት ድጋፍ
- እኛን ለማነጋገር እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች

ቀደም ሲል የወጡ መረጃዎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፦ www.gov.uk/grenfell-community-updates

**ክሬኑን ዝቅ የማድረግ ሂደት** ባለፈው በጋ በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ጣቢያ ላይ ተተክሎ የነበረው ክሬን፣ የአየር ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነ በፌብሩዋሪ ወር የትምህርት ቤት የዕረፍት ጊዜ ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

**የግሬንፌል የልብ ቅርፅ ያላቸው ባነሮች**
የግሬንፌል ታወርን በጥንቃቄ የማውረድ ስራ እየተከናወነ ባለበት ወቅት፣ ባነሮቹን ወደ ታወሩ ዝቅ አድርገን አንቀሳቅሰናል።

**የታወሩ መብራቶች**
ህንጻው በጥንቃቄ እየፈረሰ ባለበት ወቅት፣ የሚታይ ማስታወሻ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን ሰምተናል። የብርሃን ጨረሮች በየምሽቱ ከ5pm በፊት እስከ 11pm ድረስ በእያንዳንዱ የታወር ጥግ ላይ፣ እንዲያበሩ መብራቶችን አስገብተናል። በግሬንፌል የልብ ቅርጽ ባነሮች ላይ የሚያበሩት መብራቶች ደግሞ በየቀኑ ጸሐይ ከጠለቀችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ምሽቱ 11pm ድረስ ይበራሉ።

**ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የሚደረግ ክትትል መረጃ**
መንግሥት በግሬንፌል ታወር ጣቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም ሥራዎች በከፍተኛ ጥራት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የማህበረሰቡ እና በጣቢያው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ደህንነት እና ጤንነት ሁልጊዜም ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በጣቢያው ላይ ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የቀጥታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ የክትትል መሣሪያዎች ተተክለዋል። መረጃው በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶችን ለማየት፣ እባክዎን ከታች ያሉትን ሊንኮች ይጫኑ፦

የአቧራ ክትትል ሪፖርት፦ ከጃንዋሪ 5 እስከ ፌብሩዋሪ 1፣ 2026
የንዝረት ክትትል ሪፖርት፦ ከጃንዋሪ 5 እስከ ፌብሩዋሪ 1፣ 2026

[የድምጽ ጫጫታ ክትትል ሪፖርት፡- ከጃንዋሪ 5 እስከ ፌብሩዋሪ 1፣ 2026]

የእንግሊዝ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ (UK Health Security Agency፣ UKHSA) ሥራው በሚካሄድበት ጊዜ በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ዙሪያ ያለውን የአየር ጥራት መገምገምና መከታተልን ይቀጥላል። ሪፖርቶቹ በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ። የቅርብ ጊዜውን ሪፖርት እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡-
[የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) እሳትን ተከትሎ የሚደረግ የአካባቢ ክትትል - GOV.UK]

## የጤና እና ደህንነት ድጋፍ

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ፣ ቤተሰባቸውን ላጡ፣ ከአደጋው በሂወት ለተረፉት እና በአቅራቢያው ለሚገኙ ነዋሪዎች የሥነ-ልቦና እና የአካል ደህንነት ድጋፍ መስጠቱ ይቀጥላል።

አንድ ሰው ማነጋገር ከፈለጉ፡-

- በ 020 8637 6279 ለግሬንፌል ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Wellbeing Service) ይደውሉ (በየቀኑ ከ8am እስከ 8pm)።
- ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የኤን ኤች ኤስ ፋውንዴሽን ትረስት (Central and North West London NHS Foundation Trust’s, CNWL) የአንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት መስመርን በሚከተለው አድራሻ ይደውሉ፡-
  0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)።
- ኢሜል: grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ተጨማሪ ለማወቅ እዚህ ይጎብኙ፡- www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk

ስለሚገኙ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፡- www.grenfell.nhs.uk

## እንዴት ማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል

መረጃውን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማጋራት እንፈልጋለን። በሚከተሉት አድራሻዎች ላይ በየጊዜው የሚወጡ ዝማኔዎችን እና መረጃዎችን ማጋራታችንን እንቀጥላለን፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates

እባክዎ በዚህ ኢሜይል ያድርጉልን፡- GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ወደ:

- ለእርስዎ አመቺ በሆነ ጊዜ፣ ቀን እና ቦታ በግል ወይም በቡድን ሆኖ እኛን ለማነጋገር ቀጠሮ ያስይዙ።
- ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራን በተመለከተ ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ይጠይቁን ወይም ስጋቶችዎን ያጋሩን።
- ስለ ሥራው ሂደት መወያየት የሚችሉባቸውን ከመንግሥት ባለሥልጣናት እና ከዋናው ተቋራጭ DCUK ጋር በየጊዜው የምናደርጋቸውን ስብሰባዎች በተመለከተ መረጃ ያግኙ።
- የምናወጣቸው ወቅታዊ መረጃዎች በቀጥታ በኢሜይል እንዲላኩልዎ ይጠይቁን።
- ከእርስዎ ጋር በምናደርገው የግንኙነት እና የተሳትፎ ሂደት ላይ ያለዎትን አስተያየት፣ ፍላጎትዎ ከሆነ፣ ያጋሩን። የእርስዎን ሃሳቦች በደስታ እንቀበላለን።

ስለ ግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎች እንዲደርስዎ ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደ www.gov.uk/grenfell-community-updates ይሂዱ ወይም የQR ኮዱን ይቃኙ።

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ጣቢያ አስተዳደር ቡድን፣**

**የቤት፣ የማህበረሰብ እና የአካባቢ መንግሥት ሚኒስቴር**